# <u>ይኼ......የማነው ?</u>

## የስድስቱ ተዋንያን ገጸ-ባኅሪያት ፤

በአቤ ኮስትሬ ፡

የተዋንያኑን ግላዊ አገላለጽ ከማስቀመጤ በፊት ፤ ስማቸውን ማለት የፈለጉትንና ለዚያም ያነሳሳቸውን ምክንያት በሚከተለው አስቀምጣለሁ ።

እኛ ኢትዮጵያዊያን ባሳለፍነው ታሪካችን ውስጥ አንድ ያላተኮርንበትና እርግፍ አድርገን ልንተወው ያልቻልነው ነገር ቢኖር ፤ በንግግር ያለመጣጣም ፤ ያለመግባባት ጉዳይ ነው ። ይህ ደካማ አስተሳሰብ ጎልቶ የታየብን ለመሆኑ ከዘመነ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ማክተም በኋላ ያሳለፍነው የፖከቲካው መፍትሔ አልባ ጭቅጭቅ የቅርብ ጊዜው ትዝታና ምስክር ነው ። ይህንን አባባል የሚደግፈው ወገን እጅግ በርካታ ሲሆን ፤ ምናልባትም ጥቂቱ ያስተባብል ይሆናል ። የዚህ በንግግር አለመጣጣምና አለመግባባት ጉዳይ በግለሰብ ውይይት ብቻ ሳይሆን ፤ በመራኄ መንግሥት ፓርላማ አባላት ፤ በፖለቲካ ፓርቲዎችና በዘር ድርጅት ስብስቦች ወዘተ...በገሃድ ሲታይ የቆየ ነው ።

መወያየት ግዴታና መሆንም ያለበት ነው ብለን ልናምን እንችላለን ። ዳሩ ግን ለውይይቱ መፍትሔ የማስገኘት ጉዳይ ላይ ፤ " አዋቂው እኔ ነኝ ! እኔ ያልሁት ካልሆነ የሌሎቻችሁ ሃሳብ ያስጠፋናል ! " ከሚል ስሜታዊነት የተነሳ የጉዳዮች ተንጠልጥሎ መቅረትና ፤ የታሰቡት ፕሮግራሞች ግብ ያለመምታት በየጊዜው ያሳለፍናቸው ድክመቶቻችን መሆናቸውን የሚክድ ያለ አይመስለኝም ። ዓላማ ወይም ፕሮግራም ሳይሳካ ሲቀር ፤ ሳይወዱ የግድ ዋሾነትንም ስለምንማር መንግሥት ነኝ ተብዬውም ውሸቱን ተለማምዶታል ።

እነዚህ ያለመግባባቶች ያደረሱብን ጉዳት ይኸን ያህል ነው ተብሎ ባይነገርም ሀብተ-ቅርሳችንን ፤ የብዙ ታጋዮችን ፤ የብዙ ጠቢባንን ሕይወት ከማስበላቱ ባሻገር ሀገሪቱ በጉልበተኞች እጅ ወድቃ የሕዝባችን ሰላማዊ ኑሮ ተቃውሷል ! ከዚህም ችግራችን ለመውጣት " እስቲ አሁን እንኳ ቀናውን መንገድ ይዘን ለመጓዝ እንሞክር " ተብሎ በቅን ሃሳቢዎች የተለያየ ጥሪ ቢደረግም ሕዝቡን የሆነ አዚም እየተፈታተነ እንደሆነ እንጃ ለኔ ግልጽ አይደለም ። አሁንም በዚያው ያለመግባባትና የውሸት አረንቋ ውስጥ እየዳከርን ነው የምንገኘ ።

ስድስቱ ተዋንያን የተለያየ አመለካከታቸውን ለማሳየት የፈለጉት ፤ ከላይ የተገለጸውን ለማንጸባረቅ ሲሆን ፤ የተዋንያኑም ስማቸው የሚከተለው ነው ።
1/ ተስፈኛው 2/ ተስፋ የቆረጠው 3/ ተስፋ አስቆራጭ 4/ ብሶተኛው 5/ ታዛቢው 6/ አዛኙ ይባላሉ ። ለመነጋገሪያው መነሻ የሆናቸው ምክንያት ከላይ የተገለጸውና ፤ እንዲሁም የቀድሞውን የኢትዮጵያ ካርታ በተመለከተ ነው ።

በዚህም ተባለ በዚያ ፤ አንዳንዶቻችን የኢትዮጵያን ማደግና ብልጽግና ስንመኝና ተስፋ ስናደርግ ፤ ሌሎች ወገኖች ደግም ከቀንደኛ ጠላቶቻችን ጋር በማበር ፤ ሆድ አደር በመሆንና ሕዝብን ተስፋ በማስቀረጥ ፤ አንዳንዱም ታግሎ ለድል መብቃት እያቻለ ፤ ነገር ግን በኢትዮጵያዊነት ላይ ተስፋ ቆርጦና የራሱን ነፃነት ራሱ ረግጦ ሌሎችን ተስፋ ሲያስቆርጥ ፤ አንዳንዱም ወገን ከታላቅና ከሩ የኢትዮጵያዊ ዜግነት ቁልቁል ወርዶ የጎሣ ፖለቲካ ውስጥ ሲዘቅጥ ፤ አንዳንዱም ወገን ባሳለፍነው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለውጤት ሳንበቃ ረጅም ዓመታት ማሳለፋችን ብሶት አሳድሮበት እንደነበረ የሚያመላክት ነው ። በጥቅሉ ግን የተዋንያኑ አገላለጽ የሚያሳየን ምስል ውስጣችን እየተቀጣጠለ ያለውንና ጊዜ ያልሻረውን ደካማ አስተሳሰባችንን ፤ ብሎም በዚሁ ደካማ የሕይወት ጉዞ ጤናማ ባኅሪ ያለማንጸባረቃችንን ጭምር በመሆኑ በጥሞና እንዳስሰው ።

እዚህ ላይ ሰባተኛ ተዋንያን ሆኖ ሊጠቀስ ያላስፈለገ አንድ በትምህርቱ ያልገፋ ግለሰብ ከተዋንያኑ ጋር ትውውቅ ስለነበረው ባጋጣሚ የሚወያዩበትን የቀድሞውን የኢትዮጵያ ካርታ ተመልክቶ ፤ <u>" ይኼ የማነው ? "</u> ሲል ላቀረበው ጥያቄ ተዋንያኑም እንደራሳቸው አገላለጽ ሊያስረዱት ሞክረዋል ። ስለሆነም የዚህ ሥነ-ግጥም ደራሲ "<u>ይኼ የማነው ? "</u> የሚለውን ጥያቄ ብቻ መሠረት አድርጎ ያቀረበውን በሚከተለው ጋብዟችኋል ።

## 1.ተስፈኛው

ጥያቄህ ገብቶኛል
ይኼ የማነው ሲባል !
ማንስ ቢሆን ማን
የማንስ ቢሆን
አንተን ምን ዶለህ
ምን አስጠየቀህ ?
ብዬህ መልስ ብሰጥ
በሃሳብ አትመሰጥ
ይኼ .... ያንተ የኔ
የሰፈው ወገኔ
የመጣው ከትውልድ
የሚዞር ለትውልድ
አንጡራ ሀብታችን
የመከበሪያችን
ሊሆንም ይችላል
ምን ያጠያይቃል ?
የኛ ብቻ ሳይሆን
የኛ መሆኑን ስንገኝ ይዘን !
ያኔ ታውቀዋለህ የኛ መሆኑን

መነሻውንና የመድረሻውን
ሳያውቀው ውሉን
አዕምሮውን ያጣ ተስተውሎውን
ሳይገባው ይጣላል ካገር ልጅ ወገን
ሃሳቡንም ሲገልጽ ያወቀ መስሎት
ለሞኞች ያብራራል እንዲያደንቁለት
ምንም ሰው ብንባል አንድ ዓይነት ፍጡር
እኔ ካልማገዝ ዕንቁ እናንተ ካፈር
አንድ አንሆንም ከቶ ብንመራመር
ሰው የሚሰኘው ስም በጣም ይገርመኛል
እንዴት ለሁላችን አንድ ላይ ይሰጣል ?
እኔ ከእገሌ .....ዘር
ከድንቂቱ ...መንደር
ከጀግኖቹ ጎራ ከስመ ጥሮቹ...
ከመልከ መልካሞች ከሸበላዎቹ
ከአልማዝ ዕንቁዎቹ ከዚያ ተፈጥሬ
እንዴት ከናንተ ጋር ተደመርሁኝ ዛሬ ?
ግብዝ ዘረኞቹ ሲናገሩ አያፍሩም
ስለ ሥነ-ፍጥረት የሚያውቁ አይመስለኝም
እንዲህ ዓይነት መርገምቶች
የሰው እንክርዳዶች
የሕይወት ነቀዞች ወይም ሾተላዮች
ሰላም ከየት ይምጣ እነሱ እያሉ ?
ፍቅርስ ከየት ይምጣ እነሱ እያሉ ?
ወገን እንበርታና ዓረሙን እንንቀል
ለዘለቄታችን ደጋጉን እንትከል
ይኼ...የማን መሆኑን
እንዳታውቅ ያደረጉህን
ከፋፍለው በታትነው ያሾፉብህን
ሰላምህን ተክለህ ዓረም ስትነቅል
ሁሉ ያንተ መሆኑን ታውቀዋለህ በውል !!

## 2. ተስፋ የቆረጠው

ኑሮን ስንመዝነው
ውስጡን ስናጤነው
እሱ ለራሱ ነው
አንተም ለራስህ ነው
እኔም ለራሴ ነው
እሷም ለራሷ ነው
ግን ይኼ...የኛ ነው !
ማን ለማን ይኖራል ?
ማን ለማን ይቆማል ?
ሁሉ ለራሱ ነው
የሚንከላወሰው !
ክፉም ይሥራ ደግ
ራሱን ሊያሳድግ
ሁሉም ለራሱ ነው
የሚንከላወሰው !
ይኸን የኛን ነገር
ማነው የሚመራመር ?
ሰው ሁሉ ካቆመ እንደ ሰው ማሰብ !
አይሆንም መፍትሔ ቁልሉ ሰበብ
ያንተ የሆነውን አንተ ካልጠበቅኸው
ነገ የሌላ ነው !!
ዛሬ ካመለጠ በእጅህ ላይ ያለው
በልምምጥ ለቅሶ ከቶ አትመልሰው !
ከሆነም በርትተህ
ወገብህን ታጥቀህ
ጉልበት አፈርጥመህ
አንድነትን አውቀህ
ወሬ ሳታበዛ
ዋዛና ፈዛዛ
ጥበብ  በተመላው ድንቅ ፖለቲካ
ጉደኛ ጠላትህን ማኖ  ስታስነካ !
አይቀርም አንድ ቀን ያንተን ማስመለስህ
በእጅህ ላይ ማድረግህ
የአንድነትን ጥቅም ገሃድ ሳታሳይ
እንዲያው ዘራፍ ብትል በየጎራው ላይ
ምንም አይረባህም ወገኔ አስብበት
ዘመንን በወሬ ከምትገፋበት
የምትመካበት ወገን ቤተሰብህ
ከምድር ላይ ተሟጦ እንዳይፈጅብህ
ሰውን በሰውነት ወደህ ተቀበለው
ሌሎች ይቀበሉህ አንተንም ሰው ብለው
የነገዋ ዓለም ብትሆን ድንበር አልባ
ጎሣ ዘር ቆጠራህ ፈጽሞ ሳይረባ
በኋላ እንዳታዝን በከንቱ ልፋትህ
ይታየኛልና  መፃኤው  ጸጸትህ
ቁጭት ምላጭ ሲያስውጥህ
ሕዝብ መሣለቂያ ሲያደርግህ
ለማንኛውም ይኼ... የኛ መሆኑን አውቀህ
ከኋላ-ቀር አስተሳሰብህ ተላቀቅ !!
ወድቀህ እንዳትቀር ተጠንቀቅ

## 3. ተስፋ አስቆራጭ :

አሁንኮ ጠፍቷል
የጋራ የሚባል
ራስ ወዳድነት ነው
ሁሉን ያሸነፈው
ለአንድነት እንጠንክር
ለፍቅር እንዘምር
ትልማ መሬታችን
ይሙላ ጎተራችን
ጸጋው ይትረፍረፍ
ካፍ እስተ ገደፍ
ጤንነት ይስፋፋ
ሕመማችን ይጥፋ
አሮጌ ተስፋ ነው
ለዛሬም ተረት ነው
ማን ይሰማኝ ብለህ
እንዲያው ትደክማለህ
ለሀገር ለወገን
ብንጮህ ሁላችን
ግል ነው ቀዳሚው
አንድነት አውዳሚው !

ማን ለማን ሊቆም ነው ?
ማን ማንን ሊያድን ነው ?
ራስህን ሳታድን ስታስብ ለሌላ
ላንተስ ማን ቆመልህ በግፍ ስትጉላላ ?
አንደኛው ሌላውን ማዳን ከተሳነው
አንተ ላንተ የማትሆን ከቶ ለምንድነው ?
ዕውነትን ሸሽተን
ሐሰትን ቀርበን
ዴሞን አስደቅለን
ክራሲ አስወልደን !
ሳንነቃ  ነቅተን
በሃሳባችን ባዝነን
በተግባር ደህይተን
ሌት-ከቀን ስንጮህ ከዲቃላው ጋር
ዕምነት ሃሳባችን ሳይተገበር
እኛም እኛ ሳንሆን ሀገርም ሀገር
መከራው በርክቶ
ሕዝቡ በቁም ሞቶ !
እኔማ ለምን ተስፋ አልቆርጥም
ለግሌ ብቻ ነው ሌሎች አልወክልም
ሆኖም ይኼ ...የኛ መሆኑን አልጠራጠርም
ስለዚህ ግል ነው ቀዳሚው
አንድነት አውዳሚው !

## 4. ብሶተኛው

ሰው ሁሉ ከሆነ ፖለቲካ አዋቂ
ነገር አራቃቂ
ማን ይሁን ወታደር ?
ማን ይሁን መምህር ?
ገበሬውስ ማነው ?
ነጋዴውስ ማነው ?
በዛኮ ሕመሙ
የታለ ሐኪሙ ?
የታለ መሐንዲስ ?
ማሂኛ ሚቀይስ
መንገዱን ስተን
የትም ስንባዝን !
የማናውቀውን
የምናውቅ መስሎን !
ባጉል ፖለቲካ
ነገር ስናቦካ !
እርስ በርስ ተባልተን ሀገር ስናጠፋ
አደጉ ሌቦቹ ገነኑ በይፋ !!
ይኸ...የኛ የምንለው
መጠሪያው የኛ ነው !
ጥቅሙ የሌላ ነው !! ካካካካካ
በዘር ተናንቁ
ተሰነጣጠቁ
ብሎም ፖለቲካ
ሰው በሰው ሲያቦካ !
ማንኪያ እርሾ ነገሥ !
ሊጡን አላወሰ ! ካካካካካ

ሁሉም ለራሱ ነው
የሚንከላወሰው
ካልተደማመጠ ችግሩ ካልገባው !
አይጠቅምም ለሌላው ለራሱ ያልረባው
ማይሙ ሲሳሳት ካላረመ ምሁር !
ምሁሩ ሲሳሳት ማይሙ ያስተምር ?
እንደዚያ እየሆንን ግራ ከተጋባን
ከቶ ሳንጠቀም ሀገር ወገን እያልን
ፖለቲካው ነዶ ሀገር ሲቃጠል
ወገን ችግር አንቆት ነፍሱ ሲጥ ሲል
የፖለቲካው ጢስ ሁሉንም አፍኖ
ከጢስ የተረፈው በጥይት ተዳፍኖ
በዘር ማጥፋት ሤራ የተሠማሩት
ሕዝብን ሲያዋክቡ ስናይ በትዕግሥት !
ምንድነው ምንጠብቅ ምን ይሁን አላችሁ ?
ባዕድ ስትሆኑ በገዛ ሀገራችሁ ?

## 5. ታዛቢው ፡

ታማኝ በጽናቱ
ዕቡይ በክዳቱ
ያለ ነው የሚኖር
የት አለ አዲስ ነገር ?

ማን ለማን ይቆማል?
ማን ለማን ይኖራል?
ግን እኔ አልገባኝም
ይህንን አላምንም !
አንዱ ላንዱ ባይቆም በሰብአዊነት
ባይደጋገፉ ሕዝብና መንግሥት
አንዱ ላንዱ ባይኖር
የት ነበር የሰው ዘር ?
ተፈጥሯዊው ሕግ
ያን ባይደነግግ
ተዋልዶ ተፋቅሮ
አንዱ ሌላው ጋር
መች ይኖር ነበር ?
በርግጥ አሁን እንደማየው
ለበስባሽ ሥጋ ነው
ሁሉም የሚያስበው !!
ሀገርን መውደድ
በአፍአዊ ልማድ
ወገን ስናፈቅር
በማስመሰል ፍቅር
ገሃድ ወጣ ዕውነቱ !!
የዛሬና የጥንቱ !
በርግጥ አሁን እንደማየው
ግል ነው ቀዳሚው
አንድነት አውዳሚው !
ሳይሆን እንደ ቀድሞው
ዛሬ እንዳየነው
በድሃው ሕዝብ እንባ
ቤቱን ያልገነባ
ከቶ ማነውሱ
ሥልጣኑ ትራሱ
ያልቆመ ለራሱ ?
ተምሮ ያልተገራ
ሁሌ ዘር ቆጠራ
ዜግነትን ንቆ
ዘር በዘር ተናንቆ
ፖለቲካ አንድዶ
አንድነቱን ማግዶ
ሕዝባችን ሥዕሉ
ይህንን መምሰሉ
ዓለም አስደንቋል !
ታዲያ ምን ያደርጋል ?
ሆኖም ይኼ ...የማነው ? ያልኸው !
ይኼማ.... የኛው ነው !!

## 6. አዛኙ ፡

ጥያቄህ ገብቶኛል
ይኼ....የማነው ይላል
ያንተ ለመሆኑ ላንተ ካልገባህ
እንዴት ላስረዳህ ?
ይኼ ....የማነው ያልኸው
ካርታው ?
ሉዓላዊነትን ያቀፈው ?
በጥቅሉም ሀገሩ ወንዙ ባሕሩ ?
ተራራ ሸንተረሩ ?
አዕዋፋት አራዊቱ ?
ዕጸዋት ሁሉ እንስሳቱ ?
ላንተ የተሰጠ ! ያንተ ነው !
ወደፊት ስህተትህን ካላረምኸው
ያገር ልጅ ወገንም ያንተው ነው !
በነገድ በጎሣ ካልበተንኸው
ማንም ሆነ ማን
ሀገር ላያድን
ወገን ላይጠግን
ሕማም ላይፈውስ
ሀገር ላያድስ !
እንባ ላያብስ !
ዝም በለው ይናከስ !
እስኪገባው ድረስ
የኑሮ ትርጉሙ
ሀገር ወገን ጥቅሙ
እስኪገባው ድረስ
ዝምበለው ይናከስ !
ስንል በጭካኔ !
ከዚህ የበለጠ ምናለ ኩነኔ ?
አውቆ አጥፊውን መውቀስ
የሳተን መመለስ
ተምሮ ማስተማር
የምሁሩ ተግባር
መሆኑን ስናውቀው
ምንድነው ጭካኔው ?
ሆኖም ጥልቅ አዕምሮ ላለው
ይኼ...ግን የኛ ነው
የኛ የሆነውን እኛ ካልጠበቅነው
ነገ የሌላ ነው
ሥልጣኑ ፖለቲክ ለማያስጨንቀው
ላገር ለወገኑ ቁጭት ለሚሰማው
ተምሮ ሊያስተምር ቁርጠኛ ለሆነው
የመረረውን ሂስ አምኖ ለሚጋተው
ሀገር ሕዝቡን ሊያድን ቆርጦ ለተነሳው
ይኼኮ.....የኛ ነው !!
ይህንን መከራ ለልጅህ ብታወርስ
ተጠያቂኮ ነህ  ነገ በሥጋ ነፍስ
ስለዚህ ወገኔ አስብ ቆም ብለህ
ኋላ-ቀር ልማድህ አንቆ ሳይገድልህ !!